**מדינת ישראל**
**משרד החינוך**
סוג הבחינה: בגרות
מועד הבחינה: חורף תש"ף, 2020
**מספר השאלון: 029284**
נספחים: גלויה (לשאלה 6)
כרזה (לשאלה 7)
**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה דתי

## לעולים חדשים

## בבתי ספר דתיים

**הוראות לנבחן**

א. <u>משך הבחינה</u>: שעתיים וחצי.

ב. <u>מבנה השאלון ומפתח ההערכה</u>:

בשאלון זה שלושה פרקים.

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | (13x3) | — | 39 נקודות |
| פרק שני | — | (22x1) | — | 22 נקודות |
| פרק שלישי | — | (13x3) | — | 39 נקודות |
| סה"כ | | | — | 100 נקודות |

ג. <u>חומר עזר מותר בשימוש</u>:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. <u>הוראה מיוחדת</u>:

בתשובתך הבא <u>עובדות</u> ואל תסתפק בהערכות כלליות.

כתוב <u>במחברת הבחינה בלבד</u>. רשום "טיוטה" בראש כל עמוד המשמש טיוטה.
כתיבת טיוטה בדפים שאינם במחברת הבחינה עלולה לגרום לפסילת הבחינה.

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

**እስራኤል አገር**
**የትምህርት ሚኒስቴር**
የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና
የፈተናው ጊዜ፦ የ2020 ዓ.ም. የክረምት ፈተና
**የፈተናው ቁጥር፦ 029284**
አባሪዎች፦ ፖስት ካርድ (ለጥያቄ 6)
ማስታወቂያ (ለጥያቄ 7)
**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የሃይማኖት ታሪክ

## ለአዲስ ገቢዎች

## በሃይማኖተኞች ት/ቤቶች ለሚማሩ

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

ኢ. <u>ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ</u>፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב. <u>የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ</u>፦

ይህ ፈተና ሦስት ምዕራፎችን ይዟል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — | (3×13) | — | 39 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | — | (1×22) | — | 22 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሦስት | — | (3×13) | — | 39 ነጥብ |
| በአጠቃላይ | | | — | 100 ነጥብ |

ג. <u>ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ</u>፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. <u>ልዩ መመሪያ</u>፦

በመልስህ ላይ ተጨባጭ <u>እውነታዎችን</u> አሳይ፥ ጠቅለል ባለ መልስ አታብቃ።

<u>በመጠይቁ ደብተር ላይ ብቻ</u> ጻፍ። ለማስቢያ በምትጠቀምበት ገጽ መግቢያ ላይ በሙሉ "טיוטה" ብለህ ጻፍበት።
ከመጠይቁ ደብተር ውጭ በሆነ ወረቀት ማስቢያ መጻፍ ለፈተናው ውድቅ መሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

# ጥያቄዎቹ

## ምዕራፍ አንድ (39 ነጥብ)

ከ1-5 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)።

**1.** አምኒሲፓሲያ በይሁዳውያን ላይ ያለውን ሁለት ተጽኖዎች **አቅርብ።**
ኒዮ ኦርቶዶክሶች ዘመናዊነትን እንዴት እንደተቋቋሙ **አብራራ።**

**2.** ለአንደኛው የዓለም ጦርነት መፈንዳት ምክንያት የሆነው አንዱ አውሮፓን ለሁለት ተቃዋሚ ጎራዎች የከፈላት የጥምረቶች ሥርዓት (מערכת הבריתות) ነው።
የጥምረቶችን ሥርዓት **አቅርብ።**
ለአንደኛው የዓለም ጦርነት መፈንዳት ምክንያት የሆነ አንድ ተጨማሪ መንስኤ **አቅርብ።**

**3.** በመጀመሪያው አሊያ (ወደ እስራኤል ሀገር መግባት) አዲስ ገቢዎች የተቋቋሟቸውን ሁለት ችግሮች **አቅርብ።**
እነዚህ አዲስ ገቢዎች ለእስራኤል ሀገር የይሁዳውያን ሠፈራ መስፋፋት ያደረጉትን አንድ አስተዋጽኦ **አቅርብ።**

**4.** ከ1936 እስከ 1939 (תרצ"ו-תרצ"ט) ባሉት ዓመታት፣ የብሪታኒያ መንግስት ለምን ከይሁዳዊያን ሠፈራ ጋር እንደተባበረ **አብራራ።**
ለዚህ ትብብር አንድ ምሳሌ **አቅርብ።**

**5.** ከሦስተኛው (1939) ነጩ መጽሐፍ ውስጥ ሁለት አንቀጾችን **አቅርብ።**
ካቀረብካቸው አንቀጾች በአንዱ መሠረት የሦስተኛው ነጩ መጽሐፍ የብሪታኒያውያን መመሪያ ከባልፉር (1917) ድንጋጌ መመሪያቸው እንዴት እንደሚለይ **አብራራ።**

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## **ምዕራፍ ሁለት** (22 ነጥብ)

ከ6-7 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

### 6. **የይሁዳዊ ብሔርተኝነት መሥፋፋት**

**አ.** የ"አፍቃሪ ጽዮን" ("חובבי ציון") ድርጅቶች የተቋቋሙበትን አንድ መንስኤ **አቅርብ።**
የ"አፍቃሪ ጽዮን" ድርጅቶችን ዓላማ ለማራመድ ፒንስኬር ያደረገውን አንድ ድርጊት **አብራራ።**
(10 ነጥብ)

**ለ.** ለአምስተኛው የጽዮናውያን ኮንግረስ ክብር (1901) የወጣው ፖስት ካርድ (ፎቶግራፍ ያለው ደብዳቤ) በጥያቄ 6 አባሪ ላይ ቀርቧል።
በፖስት ካርዱ ላይ የሕዝበ ይሁዳውያን ችግር የነበረው ጸረ-ይሁዳዊነት እና የጽዮናውያን ንቅናቄ (תנועה) ያቀረበው መፍትሄም ተግባራዊ ሆነዋል።
በፖስት ካርዱ ላይ ካሉት ጥንቅሮች በአንዱ መሠረት ጸረ-ይሁዳዊነት እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን **አብራራ።**
የጽዮናውያን ንቅናቄ ያቀረበው መፍትሔ ምን እንደነበር **ጥቀስ።**
በፖስት ካርዱ ላይ ካሉት ጥንቅሮች በአንዱ መሠረት ይህ መፍትሔ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን **አብራራ።**
(12 ነጥብ)

### 7. **ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ብሪታንያውያንን መታገል።**

**አ.** "הלפעה" ን በተመለከተ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በይሁዳውያን ሠፈራዎች የተሰራጨው ማስታወቂያ/ነጋሪት ጋዜጣ በጥያቄ 7 አባሪ ላይ ቀርቧል።
በነጋሪት ጋዜጣው መሠረት፦ የ"הלפעה" ን ድርጅት ዓላማ **አቅርብ።**
ይህ ዓላማ በነጋሪት ጋዜጣው ሁለት ጥንቅሮች መሠረት እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን **አብራራ።**
በተማርከው መሠረት፦ብሪታኒያውያን የ"הלפעה" ን ድርጅት ለመታገል የሞከሩባቸውን ሁለት መንገዶች **አቅርብ።**
(15 ነጥብ)

**ለ.** በተማርከው መሠረት፦ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከ"הלפעה" ውጪ የሠፈራው ይሁዳውያን ብሪታኒያውያንን በመቃወም የታገሉበትን ተጨማሪ መንገድ **ጥቀስ** እና ለዚህም አንድ ምሳሌ **አቅርብ።** (7 ነጥብ)

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሦስት (39 ነጥብ)

ከ8-12 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (እያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)።

**8.** የአፕሪል 1, 1933 አግላይ አድማው (חרם)፣ ለአንድ ቀን ብቻ ቀጥሏል። ቢሆንም በናዚዎች ዓይን ይህ አስፈላጊ ነበር።

በናዚዎች ዓይን የዚህን አግላይ አድማ አስፈላጊነት **አቅርብ።**

በአሥራ ዘጠኝ ሰላሳዎቹ ዓመታት በጀርመን ውስጥ ይሁዳውያንን በኢኮኖሚ ዘርፍ የጎዳውን የናዚዎች ሌላ ድርጊት **አቅርብ።**

**9.** በ"ሾአ" ወቅት ራባናት (የይማኖት መሪዎች) ሃላኻን (የሐይማኖት ሕግን) ለማውጣት/ለመደንገግ

የነበሩባቸውን ሁለት ችግሮች **ጥቀስ።**

በ"ሾአ" ወቅት የተነሳውን አንድ የሃላኻ (የሐይማኖት ሕግ) ጥያቄ እና ራቡ (የሐይማኖት መሪው) ለዚህ ጥያቄ የመለሱትን መልስ **አቅርብ።**

**10.** የነጻነቱ ጦርነት ባለቀ ጊዜ ከእስራኤል ሀገር ጋር የጦርነት ማቆም ስምምነት ካደረጉት የአረብ ሀገራት ውስጥ የአንዷን ስም **ጥቀስ።**

የፈረመችበትን ስምምነት ይዘት ዝርዝር **አቅርብ።**

ከነጻነቱ ጦርነት በኋላ የአረብ ሀገሮች እስራኤል ሀገርን ለመታገል የሄዱበትን ጦርነት ያልሆነ ሌላ መንገድ **አቅርብ።**

**11.** በታላቁ አሊያ ዓመታት (በአሥራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ) በአዲስ ገቢዎቹ እና በእስራኤል ሀገር ነዋሪዎች መካከል ብዙ ልዩነቶች ነበሩ።

በአዲስ ገቢዎቹ እና በእስራኤል ሀገር ነዋሪዎች መካከል በወቅቱ በነበሩት ልዩነቶች ምክንያት የነበረውን የሀገሪቱን መሪዎች ጭንቀት **አቅርብ።**

እነዚህን ልዩነቶች ለመቋቋም የሀገሪቱ መሪዎች በ"כור ההיתוך" መመሪያዎች አማካኝነት እንዴት እንደሞከሩ **አብራራ።**

**12.** ከኦስሎ ስምምነት ውስጥ ለእስራኤል ሀገር ቃል የተገባላትን አንድ ነገር አቅርብ እንዲሁም ከዚህ ስምምነት ውስጥ አንድ የባ"ሠአን ግዴታ **አቅርብ።**

የኦስሎን ስምምነት ተቃዋሚዎች አንድ መከራከሪያ ነጥብ ወይም የደጋፊዎቹን አንድ መከራከሪያ ነጥብ **አቅርብ።**

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך

# የጥያቄ 6 አባሪ — ፖስት ካርድ




(እነሆ በምህረት ወደጽዮን እንድትመለስ ዓይኖቻችን ይጠባበቃሉ)

(R. Arbel(ed.), Blue and White in Color-Visual Images of Zionism, 1897-1947, Tel Aviv, Beth Hatefutsoth, the Nahum Goldman Museum of the Jewish Diaspora, p. 17.)

## የጥያቄ 7 አባሪ — ማስታወቂያ




(ጽዮን፣ ስውር አዲስ ገቢዎችሽን አትጠይቂምን ["መአፐሊም", מעפיליך]
የአዲስ ገቢዎች ሳምንት - ዋጋ ከፍሎ እስረኞችን ማስለቀቅ)

(R. Arbel(ed.), Blue and White in Color-Visual Images of Zionism, 1897-1947, Tel Aviv, Beth Hatefutsoth, the Nahum Goldman Museum of the Jewish Diaspora, p. 48.)